**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**የኅብረት ሥራ ማህበራት (ማሻሻያ) አዋጅ አዘገጃጀት መግለጫ**

**ጥቅምት 2018 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

መግቢያ

በገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት በዘመናዊ መልክ ተደራጅተው እንቅስቃሴ ከጀመሩ ከስድስት-አስርት ዓመታት በላይ ያስቆጠሩ ሲሆን የአባላትን እና የሀገርን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በመቅርፍ ከፍተኛ አስተዋጾ ሲያበረክቱ ቆይተዋል፡፡ በተለይ የግብርና ምርት እና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የግብርና ምርት ማሳደጊ ተክኖሎጂ አቅርቦትና ስርጪት፣ የምርት ግብይትን ለማሳለጥ፣ ምርትን እና ሸቀጦችን በተመጣጠኝ ዋጋ ለአባላት በማቅርብ ፣ ቁጠባን በማበረታታት እና በተመጣጣኝ ወለድ ብድር በመስጠት አባላት ወደ ኢንቨስትመንት እንዲገቡ በማድረግ የፋይናስ ተደራሽነትን እና ተጠቃሚነትን እውን በማድረግ፣ የመኖሪያ ቤት ችግርን በመቅረፍ ፣ ከተማና ገጠርን በማስተሳሰር እንዲሁም አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚያደርጉት አስተዋጾ እንደ ሀገር ጎልቶ የሚታይ ተግባር ነው፡፡

የኅብርት ስራ ማህበራት ህግ እና ሀጋዊነትን አክብረው እንዲሰሩ የኢንስፔክሽን ፣ የህግ ፣የኦዲት እና በደረጃ በመለየት በአባላት እና በሶስተኛ ወገኖች ታዓማኝነት ሀጋዊነታቸውን እና ደህንነታቸውን የማስጠበቅ ሰራ በመስራት የኅብርት ስራ ማህበራቱ አባላትን እና ሀገርን ተጠቃሚ ማድርግ ተችሏል፡፡

በአሁኑ ጊዜ አገልግሎት ላይ ያለው የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አሁን ባለበት ደረጃ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ የተቀመጡ የለውጥ አቅጣጫዎች የብዘሃ-ዘርፍ ኢኮኖሚ፣ አገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም፣ የግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ ለውጥ፣ አገራዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት እድገትና ተወዳዳርነት ማሻሻያ ሪፎርም እና አገራዊ ኢንሸትቮች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ለማድረግ አዋጁን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተግኝቷል፡፡

በተጨማሪም የኅብረት ሥራ ማህበራትን አደረጃጀት ለማሻሻል፣ አሰራራቸውን፣ አመራራቸውና የአገልግሎት አሰጣጣቸውን ለማጠናከርና ለማዘመን፣ የገበያ ተወዳዳሪነታቸውን ለማሳደግ፣ የፋይናንስ ችግሮቻቸውን ለማፍታት እና ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት ለመዘርጋት እና ለማዘመን እንድሁም ሴቶች እና ወጣቶችን አባል እንዲሆኑ ለማድርግ በስራ ላይ ያለው አዋጅ መሻሻል አስፈላጊ ሆኗል፡፡

በዚህ መሠረት በአዋጁ ውስጥ አላሰራ ያሉ ከልካይ የሆኑ ድንጋጌዎችን ፈቃጅ ለማድረግ ፣ ፈቃጅ የሆኑ እና አላሰራ ያሉ የህግ ድንጋጌዎችን አስገዳጅ ለማድርግ እና አሁን ከደረስንበት እድገት እና የለውጥ ጉዞ አንጻር አዲስ መካተት ያለባቸው ድንጋጌዎች እንዲካተቱ አስፈለጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 ረቂቅ ማሻሻያ አዋጅ ተዘጋጅቷል፡፡

ይህ የኅብረት ሥራ ማህበራት 985/2009 ረቂቅ ማሻሻያ አዋጅ ያካተታቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ውስጥ የመግለጫው አዘገጃጀት፣ ማሻሻያ ያስፈለገበት ምክንያቶች፣ በጥናት የተለዩ የህግ ማዕቀፍ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች፣ የአዋጁ ማሻሻያ የሚያተኩሩባቸው ድንጋጌዎች አጭር መግለጫ በማካተት ተዘጋጅቷል፡፡

## 1. <u>የረቂቅ አዋጅ ማሻሻያ አዘገጃጀት</u>

የኅብረት ሥራ ማህበራት ረቂቅ ማሻሻያ አዋጅ በግብርና ሚኒስቴር አማካኝነት እየተመራ ከሚኒስቴሩ እና ከተጠሪ ተቋማት እንዲሁም ኅብርት ስራ ኮሚሽን በባለቤትንት ሆነው ሚኒስቴሩ የሚመራ የስትሪን ኮሚቴ፣ የቴክኒክ ቡድን እና የጥናት ቡድን በማቋቋም ሰፊ ጥናት በማድርግ የረቂቅ አዋጁ እንዲዘጋጅ እና ከባለድረሻ አካላት ጋር ወይይት በማድርግ ግብአቶችን በማካተት በግብርና ሚኒስቴር ማኔጂመንት ታይቶ ረቂቅ ማሻሻያ አዋጁ ተዘጋጅቶ አቅርቧል፡፡

## 2. <u>አዋጁን ማሻሻል ያስፈለገበት ዋና ዋና ምክንያቶች</u>

### 2.1. <u>አገራዊ ለውጦች</u>

የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ቁልፍ የማሻሻያ እርምጃዎች መካከል በአርሶ-አርብቶ አደሮች፣ በንግዱ ማሕበረሰብ እና በንግድ እሴት ሰንሰለት መካከል ውጤታማ ግንኙነት ለመፍጠር የኅብረት ሥራ ማህበራት ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንደሚበረክቱ ተመላክቷል፡፡ ውጤታማ የገበያ መሠረተ-ልማት አለመኖሩ፣ በገበሬዎች እና በገዢዎች መካከል ያለው የገበያ ትስስር ውስንነት ችግሮችን ለመቅረፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት ትልቅ ድርሻ የሚያበረክቱ ተቋማት እንደሆኑ ተቀምጧል፡፡

የግብርና ምርት ግብይት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ የግብይት ስርዓት መገንባት (ኤሌክትሮኒክ-ክፍያን ጨምሮ) እንደሚገነባ ተመላክቷል፡፡ የግብርና ምርቶች የግብይት ችግር ለመቅረፍ የግብርና ምርቶች የደረጃ አሰጣጥ፣ የምስክር ወረቀትና የመከታተያ አሰራርም ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን በስፋት ተመላክቷል፡፡

የአገራችንን የፋይናንስ አካታችነት (Financial Inclusion) ችግር ለመፍታት መንግስት ዘርፈ ብዙ አቅጣጫዎችን አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ አቅታጫዎች መካከል የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን በማጠናከር በፋይናንስ ዘርፉ ላይ የራሳቸውን አስተዋጽዖ ማድረግ እንዳለባቸው ነው፡፡ በመሆኑም እንደዚህ ያሉ የሕግ ማዕቀፎች ለእድገቱ እንቅፋት በማሆን ላይ ስለሆኑ ማሻሻያ እንደሚያስፈልገው በጥናት ተለየቷል፡፡

### 2.2. <u>አገራዊ አዳዲስ የልማት ኢኒሼቲቮች</u>

የሌማት ትሩፋት አርሶ-አርብቶ አደሩን እና ሸማቹን የሚያገናኝ ድልድይ ከመሆኑ በተጨማሪ በቂ እና ተመጣጣኝ ምግብ ለማግኘት እንዲቻል የተቀመጠ አቅጣጫ ነው፡፡ ዋና ግቡም የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥና የምግብ ስርዓትን ማሻሻል ነው:: ለአርሶ-አርብቶ አደሩ የስራ ዕድሎችን የመፍጠር፣ የወጪ ንግድን ማሳደግ እና ከውጭ የሚገቡ የእንስሳት ተዋፅኦዎችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት ዓላማ ያለው ነው:: የኅብረት ሥራ ማህበር ምርቱን በማምረት እና የተመረተውን

ምርት በማሰባሰብ እና እሴት በመጨመር ለገበያ በማቅረብ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንድያበረክቱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የበጋ መስኖ ስንዴ ምርት ራሳችንን ከመቻል አልፎ ለኢንዱስትሪና ለወጪ ንግድ በቂ ምርት ለማቅረብ እንዲቻል ለስንዴ ልማት ከፍተኛ ትኩረት ተሠጥቶ ርብርብ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ለዚህም መሰረታዊ የስትራቴጂ አቅጣጨዎች ተቀምጠዋል፡፡ የመስኖ ልማትን ለማጠናከርና ለማስፋፋት ከተጠቆሙ ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች መካከል የመስኖ ተጠቃሚዎችን በኅብረት ሥራ ማህበራት ማደራጀት፣ ጠንካራ የገበያ ትስስር ሥርዓት መፍጠር፣ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸው የመስኖ ሰብሎች የእሴት ሰንሰለት ማጠናከርና የመስኖ ልማቱን ማዘመን፣ የአምራች አስመራች ውል ሞዴል በመተግበር ለሀገራዊ ምርት እድገት የበኩላቸውን እንዲወጡ ማስቻል ነው፡፡

## 2.3. <u>በአዲሱ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊስ የተቀመጡ አቅጣቻዎችን የህግ ማዕቀፍ አውጥቶ ለመፈጸም</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች እና ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትና ስርጭት፣ የሀገር ውስጥ እና የወጪ ንግድ ምርቶች ግብይት፣ የግብርና ሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎት፣ የገንዘብ ቁጠባና ብድር አገልግሎቶችን ማቅረብ፣ ምርቶቻቸውን በማሰባሰብና በማከማቸት የመጋዘን አገልግሎት እንዲሁም የምርት ደረጃ መለየትና ማሸግ አገልግሎት በመስጠት ጥራቱን የጠበቀ ምርት እንዲያመርቱ ፣ የኦዲት ፣ ኢንስፔክሽን አገልግሎት በማጠናከርና በማዘመን ህግ አክብረው የሚሰሩ እና የብቃት ደረጃቸው የተለዩ ኅብረት ስራ ማህበራት፣ መገንባት እና ማጠናከር እንደለባቸው የአቅጣጫ ተቀምቷል፡፡ አላስፈላጊ የገበያ ሰንሰለትን በማሳጣር የአርሶ-አርብቶ አደሩ ምርት የተሻለ ዋጋ እንዲያገኝ ማድረግ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን ፖሊሲ ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

ይሁን እንጂ የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራርና አስተዳደር ሥርዓት ጠንካራ አለመሆን፣ ወጣቶች የኅብረት ሥራ ማህበራት አባል እንድሆኑ የሚያበረታታ ድንጋጌ አለመኖር፣ በነፃ ገበያ ሥርዓት ውስጥ መወዳደር አለመቻል ችግር በስፋት ይታያል፡፡ አማራጭ የፋይናንስ አቅርቦት እና ኢንቨስትመንትን የሚያመቻች ተቋም አለመኖር፣ የኦዲት፣ የኢንስፔክሽን እና የብቃት ደረጃ የእውቅና አሰጣጥ በተሟላ የህግ ማዕቀፍ እና አሰራር ሥርዓት አለመደገፍ፣ የግብርና ምርቶች የግብይት ድርሻ አነስተኛ መሆኑ፣ በወጪ ንግድ ላይ ያላቸው ድርሻ በመጠን ውስን መሆኑ እንዲሁም የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን እና የፍጆታ ምርቶችን ከውጪ በጅምላ ለማስገባት በቂ አቅም ባለመኖሩ የተነሳ ያላቸው ተሳትፎ በሚፈለገው ደረጃ አለማደጉን እንዲሁም የኅብረት ሥራ ማህበራቶቹ በተሳተፉባቸው የግብርና እና የፍጆታ ምርቶች አቅርቦት ላይ የመጠን፣ የጥራት እና የወቅታዊነት ጉድለቶች መኖራቸውን ፖሊሲው አስቀምጧል፡፡

2.4. <u>የአረንጓዴ ልማት እና የአየርንብርት ለወጥ ጥበቃ</u>፡-

ሀገራችን በአረንጓዴ ልማት እና በአየር ንብረት ለውጥ ጥበቃ ለምታደረገው ከፍተኛ እንቅስቃሴ የተፋሰስ የኅብርት ስራ ማህበራት እና የደንልማት ኅብረት ስራ ማህበረት ከፍተኛ አስተዋጾ እንዲያደረጉ ታሰቢ በማድርግ እንዲደረጁ እና  እንዲጠናከሩ ዘላቂ ልመት በማምጣት የከርቦን ንግድ እና የቱረስት መሰብ ሆነው የወጭ ምንዘሬ እንዲያሰገኙ እና ውብ አከበቢ በመፍጠር  አባላትን ተጠቃሚ እንዲያደረጉ ታሰቢ በማድርግ የህግ ማሻሻያው እንዲሻሻል ሆኗል፡፡

3. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 ያለበትን ክፍተት ለመለየት የተደረጉ ጥናቶች</u>

በኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን እንስቲትዩት (ATI) አማከኝነት  በአደረጃጀት ፣ በውስጥ አስተዳደር ፣ በገቢያ ተወዳደሪነት ፣ በፋይናስ አቅረቦት ፣በኅብረት ስራ የኢንስፔክሽን እና የኦዲት ተደረሽነት እና በኅብረት ስራ አዋጅ ላይ የጥናት ቡድን ከላይ በተጠቀሱት ነጥቦች ላይ የዴስክ ግምገማ ጥናት (Desk review)  እና ጥልቅ ጥናት (Deep dive study) በማድረግ ከሕግ ማእቀፍ አንጻር የተለያዩ ምክረ-ሃሰባች ተሰጥተዋል፡፡ የዓለም ባንክ ባደረገው የበጀት ድጋፍ ዓለም አቀፍ አማካሪ ድርጅት በኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን እንስቲትዩት (ATI) አማካኝነት በመቅጠር የተለያዩ በርካታ አለም-አቀፋዊ ተሞኩሮዎችን በጥልቀት በመተንተን ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በአዋጅ የሚፈታ እና በአሰራር የሚፈታ የሚል ምክረ-ሃሳብ መሰረት

የረቂቅ ማሻሻያ አዋጁ ተዘጋጅቷል፡፡

4. <u>በጥናት የተለዩ ዋና ዋና ነጥቦች</u>

- የኅብረት ሥራ ማህበራት የተደራጁባቸው ዓይነቶች የተበታተነና ውጤታማ ባለመሆኑ የሚታየውን ችግር ለመቅረፍ በማዋሀድ ወይም በመቀላቀል ሰብሳብ ብሎ በመደራጀት ውጤታማ የሆነ አደረጃጃት መፍጠር እንዳለባቸው በጥናት ተለየቷል፡፡
- የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጃት እርከን (መሰረታዊ፣ ዩኒዬን፣ ፌዴሬሽን) የሚታየውን የተግባራት ድግግሞሽ በማስቀረት እና አደረጃጀታቸውን ውጤታማ ለማድረግ አዋጁን ማሻሻል አስፈላግ ይሆናል፡፡
- የኅብረት ሥራ ማህበራት  ለአባላት እና አባል ላልሆኑ ሰዎች በሚሰጡት አገልግሎት ላይ በክፍያ ልዩነት በማድረግ አባላትን ለማበረታታት እንድሁም አባል ያልሆኑ ሰዎች አባል እንድሆኑ ለማድረግ እና ትርፋማ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አለበት፡፡
- የኅብረት ሥራ ማህበራትን የአመራር አካላት የዕውቀትና ክህሎት ችግር ለማፍታት እና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ በአማካሪ ባለሙያዎች መደገፍ እንደለባቸው ተቀምጧል፡፡ በግብርና ምርት ግብይት ላይ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብይት ቅብብሎሽ የተንዛዛ እና እሴት የማይጨምር በመሆኑ የኮምሽን ግብይት አሰራር በመዘርጋት ውጤታማ የግብይት አሰራር እንዲኖር ማድረግ አስፋለጊ ሆኗል፡፡

- የኅብረት ሥራ ማህበራት የካፒታል እጥረት ሲያጋጥማቸው በጥናት ላይ ተመስርቶ ተጨማሪ ዕጣዎችን አውጀ አባል ላልሆኑ ፍቃደኛ ሰዎች ዕጣ ሸጦ ካፒታላቸውን ማሳደግ እንዲችሉ ለማድረግ አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑ፣
- የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ተጨማሪ ዕጣ ገዝቶ የኅብረት ሥራ ማህበራቸውን እንዲያጠናክሩ ለማድረግ
- የኅብረት ሥራ ማህበራት ፈንድ እንዲቋቋም እና ፈንዱ የሚተዳደርበት ዝርዝር አሰራር እንድኖር እንደሚያስፈልግ በጥናቱ ተለይቷል።
- የዓለም ተሞክሮችን በመዳሰስ የተሰጡ ምክረ-ሃሳችን መሰረት በማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ ችግር የሚፈታ በኅብረት ሥራ ማህበራት መርህ የሚመራ የጋራ ኢንቨስትመንት ለመሰራት የሚያስችል የህግ ማዕቀፎች መቀመጥ እንዳለበት በጥናት ተለይቷል።
- የኅብረት ስራ ማህበራት የኦዲት አገልግሎት በመንግስት ኦዲተሮች ብቻ መሰራቱ የሚታወቅ ነው። በመሆኑም የኦዲት አገልግሎት ተደረሽ አልሆነም። ይህን ችግር ለመፍታት ህጋዊ ፈቃድ ያላቸው ኦዲተሮች በኅብርት ስራ ማህበራቱ ወጪ ኦዲት መድርግ እንደለባቸው ጥናቱ አማላክቷል ። ስለሆነም የኦዲት ተደራሽነትን ለማስፋት ፣ ብክነት እና ምዝበራን ለመከላከል እንዲቻል የአዋጁ ማሻሻያ በማስፈለጉ፤
- የኅብረት ሥራ ማህበራት ህግ ማስከበር እና ኢንስፔክሽን በሚፈለገው ደረጃ ቀድሞ መከላከል መርህን እና አደጋና ሰጋትን መሰረት አደርጎ ባለመከናወኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሃብትና ንብረት ላይ በርካታ ብክነትና ምዝበራ ይታያል ። በመሆኑም ችግሩን ለመፍታት እና ጠንካራ የኢንስፔክሽን ስርዓት በመዘርጋት እምነት የሚጣልባቸው ኅብረት ስራ ማህበራት ለመፍጠር እንዲቻል እና የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት አሰራሩን ለማጠናከር የአዋጅ ማሻሻያ ማድረግ የትኩረት አቅጣጫ ሆኗል።

5. <u>በተዘጋጀው ረቂቅ ማሻሻያ አዋጅ ላይ የተደረጉ ውይይቶች</u>

የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 ረቂቅ ማሻሻያ አዋጅ በረቂቅ ደረጃ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ሀሳቦች እንዲሰጡ እና እንዲዳብር ተደርጓል። በውይይቱ ላይ በአካል በመገኘት ረቂቅ ማሻሻያ አዋጁን በቃል እና በጽሑፍ ሀሳብ የሰጡና ያዳበሩት አካላት እንደምከተለው ቀርቧል።

1. የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ከፍተኛ አመራሮች፣ መሪ ሥራ አስፈጻሚዎችና ሥራ አስፈጻሚዎች ብዛት 24 (ሴቶች 6) ፣
2. የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ከፍተኛ ባለሙያዎች ብዛት 60 (ሴቶች 12) ፣
3. የሁሉም ክልሎች የኅብረት ሥራ ህግ ጉዳዮች እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ከፍተኛ ባለሙያዎች ብዛት 67 (ሴቶች 11) ፣
4. የሁሉም ክልሎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ኤጀንሲዎች የክልል ኃላፊዎች ብዛት 24 (ሴቶች 4)፣
5. የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራር አካላት እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ሥራ አስኪያጆች ብዛት 88 (ሴቶች 22)

6. የፌዴራል እና የክልል ባለድረሻ አካላት የተሳታፊዎች ብዛት 40 (15 ሴቶች)
7. የግብርና ሚኒስቴር የሕግ ሥራ አስፈጻሚ እና ፍትህ ሚኒስቴር ሥራ ክፍል ኃላፊዎች እና ከፍተኛ ባለሙያዎች 3 ጊዜ የተሳታፊ ብዛት 16
8. የግብርና ሚነሰቴር ማኔጂመንት አባላት 14 ( ሴት 1) ጉዳየን በማየት ግብአት በመሰጠት በግብአቱ መሰረት ተሰተካክሎ ለሚኒስቲሮች ምክር ቤት እንዲላክ ውሳኔ ሰጥተዋል።

ከላይ በዝርዝር የተመለከቱት አካላት በተለያዩ ዐውደ ጥናቶች በመገኘት እና በመ/ቤት ደረጃም በጽሑፍ አስተያየቶች የሰጡት ረቂቅ ማሻሻያ አዋጁን በሚያጎለብት መልኩ በጥቅም ላይ ውለዋል።

## 6. <u>የረቂቅ ማሻሻያ አዋጁ ትኩረት ያደረገባቸው ዋና ዋና ድንጋጌዎች</u>

1. የረቂቅ ማሻሻያ አዋጁ ማሻሻል ያሰፈለገበት ዋና ሀሳብ የያዘ መግቢያ ተዘጋጅቶለታል
2. የረቂቅ ማሻሻያ አዋጁ አንቀጽ 1 የአዋጁ አዲስ በመሆኑ አጭር ርዕስ ተዘጋጅቶለታል
3. የረቂቅ ማሻሻያ አዋጁ ማሻሻያ የተደረገባቸው ድንጋጌዎች ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 17 የሚደረሱ እና በእያንዳንዱ ንዑስ አንቀጽ ውስጥ የንዑስ ንዑስ አንቀጾች ማሻሻያ ተደረጎባቸው እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል።
4. የረቂቅ ማሻሻያ አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ የሚል ድንጋጌ በረቂቅ አዋጁ ተካቶ ተዘጋጅቷል።

### 6.1. <u>የረቂቅ አዋጁ መግቢያ</u>

የሀገራችን የኅብርት ስራ ማህበራት ዝቅተኛ ካፒታል እና የአባላት ቁጥር ያሏቸው እና ተበታትነው የተደራጁ በመሆኑ በመቀላቀል በግብይት ተሳትፏቸው እና በኢኮኖሚው ላይ ድርሻቸውን ለማሳደግ በማስፈለጉ፤

### 6.2. <u>የረቂቅ ማሻሻያ አዋጁ አጭር ርዕስ እንደሚከተለው ተቀምጧል።</u>

<u>አንቀጽ አንድ1/ አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ **"የኅብረት ሥራ ማህበራት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር -----/2018"** ተብሎ ተሻሽሏል

### 6.3. <u>"የኅብረት ሥራ ማህበራት (ማሻሻያ) አዋጅ ማሻሻያዎች።</u>

<u>አንቀጽ 2/ ማሻሻያ</u>

**1/ የአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (10) ተሰርዞ በአዲስ ንዑስ አንቀፅ (10) ተተክቷል**

10/ **"አባል"** የሚለው ቃል ትርጉም የተሰጠው ሲሆን ዋና ምክንያቱም በገጠር እና በከተማ የሚገኙ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ፣የማህበረሰብ አቀፍ ተፋሰስ ፣ የገበሬዎች ሁለገብ ፣ የእድ ጥበብ እና ሌሎችም ኅብረት ስራ ማህበራት ካፒታላቸውን ለማሳደግ በአቅረቢያቸው የሚገኙ ተቋማት አባል እንዲሆኑ ፣

በአካባቢቸው ኅብርት ስራ ማህበራት የተደረጁ ሰዎችን እንዲጠቅሙ እና ራሳቸውም ተጠቃሚ ለማድረግ እና በህግ ለመፍቀድ ትርጉሙ ተሻሽሏል፡፡

**2/ የአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (20) ተሰርዞ በአዲስ ንዑስ አንቀፅ (20) ተተክቷል**

20/ **"አግባብ ያለው ባልስልጣን"** የሚለው ሐረግ ትርጉም የተሰጠው ሲሆን ዋና ምክንያቱም የፌደራል የኅብርት ስራ ኤጀንሲ የሚለውን በ1263 /20014 መሰረት የስያሜ ለውጥ በመደረጉ "የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን" የሚለውን ለማካተት በማስፈለጉ ነው፡፡

**3/ ከአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 23 ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ 24 እና 25፣ ተጨምሯል፣ ነባሮቹ ንዑስ አንቀጽ 24 እና 25 እንደቅድም ተከተላቸው 26 እና 27 በመሆን ተሸጋሽጓል፡፡**

24. **"መቀላቀል"** የሚለው ቃል ትርጉም የተሰጠው ቃል ዋና ምክንያቱ የኅብረት ስራ ማህበራት የተበታተነውን የሰው ሀብት ፣ የካፒታል እውቀት እና ጉልበት በማሰባሰብ ጠንከራ እና ተወዳደሪ እንዲሆኑ ለማድረግ በአዲስ የገባ ትርጉም ነው፡፡

25. **"በልዩ ሁኔታ የሚደረግ ኦዲት"** የሚል ሐረግ ትርጉም የተሰጠው ሲሆን ዋና ምክንያቱም የኅብረት ስራ ማህበራት የኦዲት ተደረሽነቱን ለማስፋት እንዲቻል ፈቃድ በአላቸው ሰዎች ኦዲት የሚደረግበትን አሰራር የተደነገገ ሲሆን በልዩ ሁኔታ በመንግስት ኦዲት የሚደረጉበትን ድንጋጌ በግልጽ ማስቀመጥ በማስፈለጉ ትርጉም እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

**4/ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (5) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (5) ተተክቷል ፡፡ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (6) እና (7) ተጨምሯል፤**

በአዋጁ አንቀጽ 7 ስር የተሻሻሉት ድንጋጌዎች በዋናነት ተበታትነው የሚገኙ እና በኢኮኖሚው የተወዳደሪ ሚናቸው ዝቅተኛ የሆኑ የመሰረታዊ ኅብርት ስራ ማህበራት ስለሚደራጁበት ፣ ስለሚቀላቀሉበት ስርዓት በመዘርጋት በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ አቅማቸው በማሳደግ ተወዳደሪ እና ችግር ፈች የሆኑ ተቋማት ለመፍጠር በማስፈለጉ በአዲስ የተጨመሩ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

**5/ የአዋጁ አንቀጽ 9 ርዕስ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡**

**6/ የአዋጁ አንቀጽ 9 ከንዑስ አንቀጽ 5 ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ 6፣7 ተጨምሯል፡፡**

በአንቀጽ 9 ስር የተሻሻሉት ድንጋጌዎች በዋናነት የኅብረት ስራ ማህበራትን የስራ ክልል በግልጽ ለመደንገግ እና የስራ ክልሉን ማሻሻል የሚችልበትን አሰራር በመዘርጋት ህገ-ወጥነትን እንዳይከሰት ቁጥጥር እና ክትትል ለማድርግ እንዲቻል፡፡

**7/ በአዋጁ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ (2) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) ተተክቷል፡፡**

በአዋጁ አንቀጽ 14 ስር የተሻሻሉት ድንጋጌዎች በዋናነት ተበታትነው የሚገኙ እና በኢኮኖሚው የተወዳደሪ ሚናቸው ዝቅተኛ የሆኑ የኅብረት ስራ ማህበራት ዩኒዬን ስለሚደራጁበት ፣ ስለሚቀላቀሉበት ስርዓት በመዘርጋት በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ አቅማቸው በማሳደግ ተወዳደሪ እና ችግር ፈች የሆኑ ተቋማት ለመፍጠር በማስፈለጉ በአዲስ የተጨመሩ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

**8/ የአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (4) ፊደል ተራ (ሀ) ተሰርዞ በአዲስ ፊደል ተራ (ሀ) ተተክቷል፡፡**

**እና**

**9/ የአዋጁ አንቀጽ 21 ከንዑስ አንቀጽ (10) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (11) ተጨምሯል**፡፡ የሚሉት

በአዋጁ አንቀጽ 21 ስር የተሻሻሉት ድንጋጌዎች በዋናነት የኅብርት ስራ ፌዴሬሽን ከአባላት ዩኒዬኖች ጋር የግብይት እና የገንዘብ ልውውጥ ስላለው ገለልተኛ ሆኖ ኦዲት ማድረግ ስለማይችል ኦዲት ያደረጋል የሚለው ተግባር በመሰረዝ የኦዲት ስራን የሚያመቻች ተግባር ብቻ ይዞ እንዲቀጥል ስለተፈለገ ነው፡፡እንዲሁም ኅብርት ስራ ማህበራቱ የቦርድ አባላት በዩኒቨርስቲ ና በዘርፉን ሲመሩ በነበሩ ሙሁራን እንዲታገዙ ፈቃጅ ህግ ለማርቀቅ ስለተፈለገ ነው፡፡

**10/ ከአዋጁ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ (1) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) ፣ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ) እና ንዑስ አንቀጽ (3) ተጨምሯል፣ ንዑስ አንቀጽ (2) ንዑስ አንቀጽ (4) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡**

በአዋጁ አንቀጽ 23 ስር የተሻሻሉት ድንጋጌዎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ከግሉ ዘርፍ ጋር የሚያደርጉት የጋራ ኢንቨትመንት ለመፍቀድ እና የእውቀት፣የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኀለብት አዲስ ድንጋጌ መጨመር በማስፈለጉ ነው፡፡

**11/ ከአዋጁ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ (2) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ተጨምሯል፣ ንዑስ አንቀጽ (3) ንዑስ አንቀጽ (5) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡**

በአዋጁ አንቀጽ 24 ስር የተሻሻሉት ድንጋጌዎች በገጠር እና በከተማ የሚገኙ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራት ካፒታላቸውን ለማሳደግ በአቅራቢያቸው የሚገኙ ተቋማት አባል እንዲሆኑ ፣ በአካባቢቸው በኅብርት ስራ ማህበራት የተደራጁ ሰዎችን እንዲጠቅሙ እና ራሳቸውም ተቋማቱ የመቆጠብ እና የመበደር አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ እና በህግ ለመፍቀድ በማሰፈለጉ ፡፡

**12/ የአዋጁ አንቀጽ 27 ከንዑስ አንቀጽ (9) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (10) እና** (11) ፊደል ተራ (ሀ)፣(ለ)፣(ሐ)፣(መ)፣(ሠ) **ተጨምሯል፡፡**

በአዋጁ አንቀጽ 27 ስር የተሻሻሉት ድንጋጌዎች በቦታ ርቀት ፣ በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ ምክንያት ፍላጎት ያላቸው ግን በቅርበት በማህበሩ ተግባራት ላይ መሳተፍ የማይችሉ ሰዎች ከኅብረት ስራ ማህበራት ዕጣ በመግዛት የኅብርት ስራ ማህበሩ ካፒታል እንዲጨምር አባል ላልሆኑ ሰዎች ዕጣ ስለሚገዙበት፣ ስለመብታቸው እና ግዴታቸው በህግ ለመደገግ በማስፈለጉ፣

**13/ የአዋጁ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ (1) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (1) ተተክቷል፡፡**

በአዋጁ አንቀጽ 33 ስር የተሻሻሉት ድንጋጌዎች የኅብርት ስራ ማህበራት አባላት ቁጥር እድገት እየጨመረ በመምጣቱ ይህን በአመት ሁለት ጊዜ ይደረግ ቢባል በዙ ወጪ የሚያሶጣ በመሆኑ በአመት አንድ ጊዜ ይደርግ የሚል የህግ ማዕቀፍ በማስፈለጉ፡፡

**14/ የአዋጁ አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ (2) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (2) ተተክቷል ፣**

በአዋጁ አንቀጽ 25 ስር የተሻሻሉት ድንጋጌዎች የኅብረት ስራ ፈንድ ስለሚወሰንበት ሁኔታ በአዲስ ድንጋጌ ማስገባት በማስፈለጉ ህግ መሻሻያ ተደረጓል፡፡

**15/ የአዋጁ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ (1) ተሰርዞ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አቀጽ (1)፣(2) ፣(3)እና (4) ተጨምረዋል፣ ነባሮቹ ንዑስ አንቀጽ (2)፣(3)፣(4) እና (5) በቅድም ተከተላቸው (5)፣ (6)፣ (7) እና (8) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡**

በአዋጁ አንቀጽ 50 ስር የተሻሻሉት ድንጋጌዎች የኅብረት ስራ ኦዲት የሚደረገው በመንግስት ብቻ በመሆኑ የኦዲት ተደራሽነቱ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ እና የኅብርት ስራ ማህበራት አቅም እያደገ ስለመጣ የኦዲት ስራው በራሳቸው ወጪ ፈቃድ ባለው ሰው ኦዲት የሚደረጉበትን እና የኦዲት ተደራሽነትን እና ጥራትን ለማስጠበቅ የህጉ ማሻሻያ አስፈላጊ በመሆኑ እንዲሻሻል ተደረጓል ፡፡

**16/ ከአዋጅ አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ (4) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) ተጨምሯል፡፡**

በአዋጁ አንቀጽ 52 ስር የተሻሻሉት ድንጋጌዎች የኅብረት ስራ ማህበራት ህግን አክበረው እንዲሰሩ እና አባላትን ተጠቃሚ ለማድርግ በተለይ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራትን ስታንርዶችን በማወጣት ኢንስፔክት ማድርግ እና በኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ የተከሰቱ የአሰራር እና የሕግ ጥሰቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ስለሚወሰድብት ግልጸኝነት እና ተጠያቂነት አሰራር ለመዘርጋት እና በኅብረት ስራ ማህበራት እምነት እዲጣልባቸው ለማድርግ የህግ ድንጋጌ ማወጣት በማስፈለጉ እንዲሻሻል ተደረጓል፡፡

**17/ የአዋጁ አንቀጽ 75 ከንዑስ አንቀጽ (3) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አቀንጽ (4) ተጨምረዋል፡፡**

በአዋጁ አንቀጽ 75 ስር የተሻሻሉት ድንጋጌዎች የተቀላቀሉ ወይም እንደገና የተደራጁ የኅብረት ስራ ማህበራት እንደ አዲስ መመዝገብ እንዳለባቸው መደንገግ በማስፈለጉ እንዲሻሻል ተደረጓል፡፡

**አዋጅ ቁጥር ---- 2018**

**የኀብረት ሥራ ማህበራት (ማሻሻያ) አዋጅ**

የሀገራችን የኅብርት ስራ ማህበራት ዝቅተኛ ካፒታል እና የአባላት ቁጥር ያሏቸው እና ተበታትነው የተደራጁ በመሆኑ በመቀላቀል በግብይት ተሳትፏቸው እና በኢኮኖሚው ላይ ድርሻቸውን ለማሳደግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክረሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 55(6) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "**የኀብረት ሥራ ማህበራት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር -----/2018**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ማሻሻያ</u>

**1/ የአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (10) ተሰርዞ በአዲስ ንዑስ አንቀፅ (10) ተተክቷል**

(10) "**አባል**" ማለት በኀብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት እንደኀብረት ሥራ ማህበሩ አይነት የተደነገጉትን የአባልነት መመዘኛዎችን በማሟላት ለአባልነት ጥያቄ አቅርቦ ተቀባይነት ያገኘ ግለስብ ወይም መሰረታዊ የኅብረት ስራ ማህበር ወይም የኅብረት ስራ ማህበራት ዩኒዬን ወይም የኀብረት ስራ ማህበራት ፌዴሬሽን ወይም ህጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ነው፡፡

**2/ የአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (20) ተሰርዞ በአዲስ ንዑስ አንቀፅ (20) ተተክቷል**

(20) "**አግባብ ያለው ባልስልጣን**" ማለት የኢትዮጵያ ኀብረት ሥራ ኮሚሽን ወይም በክልል የኅብረት ሥራ ማህበራትን አዋጅ ለማስፈጸም፣ ዘርፉን ለመምራትና ለመቆጣጠር የተቋቋመ አካል ነው፡፡

**3/ ከአዋጁ አንቀጽ (2) ንዑስ አንቀጽ (23) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (24) እና (25)፣ ተጨምሯል፣ ነባሮቹ ንዑስ አንቀጽ (24) እና (25) እንደቅድም ተከተላቸው (26) እና (27) በመሆን ተሸጋሽጓል፡፡**

(24) **"መቀላቀል"** ማለት አንድን የኅብረት ሥራ ማህበር ሕልውናውን በማሳጣት አስፈላጊውን መስፈርት እንዲያሟላና ከሌላ ተመሳሳይ ዓላማና ተግባር ካለው የኅብረት ሥራ ማህበር ጋር አንድ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

(25) **"በልዩ ሁኔታ የሚደረግ ኦዲት"** ማለት የኅብረት ሥራ ማህበር የኦዲት ወጪ መሸፈን እንደማይችል ሲታመን ወይም እንዲፈርስ ሲወሰን ወይም የተደረገውን ኦዲት ለማረጋገጥ ሲያስፈልግ ወይም በፍርድ-ቤት ሲታዘዝ ወይም ስጋትና ጥቆማ ሲኖር አግባብ ያለው ባለስልጣን የኦዲት ወጪውን ሸፍኖ በልዩ ሁኔታ ኦዲተር መድቦ ኦዲት ማድረግ ነው፡፡

**4/ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (5) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (5) ተተክቷል ፡፡ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (6) እና (7 ) ተጨምሯል፤**

(5) ማንኛውም መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር እንደየክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ፣ እንደ ኅብረት ስራ ማህበራቱ ዓይነት ፣ የስራ ባህሪ ወይም የኢኮኖሚያዊ አዋጭነት፤ በቀበሌ ፣ በተቋም ፣ በወረዳ ፣ በዞን ፣ በክልል ወይም በፌዴራል ደረጃ ይደረጃሉ፤

(6) በተመሳሳይ ተግባር ላይ የተደራጁ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም ዩኒዬኖች ወይም ፌዴሬሽኖች ሊቀላቀሉ ይችላሉ፡፡

(7) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 5 እና 6 ዝርዝር አፈፃፀም መመሪያ ሊወጣ ይችላል፡፡

**5/ የአዋጁ አንቀጽ 9 ርዕስ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡**

(9) የኅብረት ሥራ ማህበር ሥም እና የሥራ ክልል፣

**6/ የአዋጁ አንቀጽ 9 ከንዑስ አንቀጽ 5 ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ 6፣7 ተጨምሯል፡፡**

(6) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተወሰነ የራሱ የሥራ ክልል ይኖረዋል፡፡

(7) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ያለው ባለስልጣን በማስፈቀድ የሥራ ክልሉን ማሻሻል ይችላል፡፡

**7/ በአዋጁ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ (2) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) ተተክቷል፡፡**

(2) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ዩኒዬን እንደየ ክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ወይም እንደ ኅብረት ስራ ማህበራቱ ዓይነት ወይም የስራ ባህሪ ወይም የኢኮኖሚያዊ አዋጭነት እየታየ በዞን ወይም በክልል ወይም በፌዴራል ደረጃ ይደራጃሉ ፤

**8/ የአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (4) ፊደል ተራ (ሀ) ተሰርዞ በአዲስ ፊደል ተራ (ሀ) ተተክቷል፡፡**

ሀ) ለአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች የኦዲት አገልግሎት ማመቻቸት፣

**9/ የአዋጁ አንቀጽ 21 ከንዑስ አንቀጽ (10) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (11) ተጨምሯል፡፡**

(11) የኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ አመራር አካላት ወይም ቦርድን የሚያማክሩ አማካሪ ባለሙያዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙን በተመለከተ መመሪያ ይወጣል፡፡

**10/ ከአዋጁ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ (1) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) ፣ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ) እና ንዑስ አንቀጽ (3) ተጨምሯል፣ ንዑስ አንቀጽ (2) ንዑስ አንቀጽ (4) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡**

(2) የኅብረት ሥራ ማህበራት ከግሉ ዘርፍ ጋር የሚያደርጉት የጋራ ኢንቨትመንት በጠቅላላ ጉባዔ ልዩ ውሳኔ እና የተቋቋሙበትን ዓላማና ተግባር መሠረት በማድረግ በሚከተሉት የኢንቨስትመንት መስኮች ላይ ይሆናል፡፡

ሀ) በግብርና ምርት ማምረት ወይም ግብይት ወይም ማቀነባበር ወይም ፋብሪካዎች ወይም ሜካናይዘሽን ዘርፍ፣

ለ) በትራንስፖርት ወይም መሰረተ-ልማት ወይም ፋይናንስ ዘርፍ፣

ሐ) በኢነርጂ አቅርቦት ወይም ኮንስትራክሽን ወይም በማዕድን ዘርፍ፣

መ) በማህበረሰብ አቀፍ ተፋሰስ ወይም የአየር ንብርት ለወጥ ወይም በቱሪዝም አገልግሎት

(3) የኅብረት ሥራ ማህበራት ከግሉ ዘርፍ ጋር ስለሚያደርጉት የጋራ ኢንቨስትመንት በሰነድ አረጋጋጭ አካል በተመዘገበ ውል ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡

**11/ ከአዋጁ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ (2) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ተጨምሯል፣ ንዑስ አንቀጽ (3) ንዑስ አንቀጽ (5) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡**

(3) ተቋማት የመሰረታዊ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለአፈጻጸሙ ዝርዝር መመሪያ ይወጣል፡፡

(4) **"ተቋም"** ማለት የአባልነት መስፈርት አሟልቶ የመሠረታዊ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አባል ሊሆን የሚችል ሕጋዊ ሰውነት ያለው መንግስታዊ ያልሆነ አገልግሎት ሰጪ ወይም አምራች ነው፡፡

**12/ የአዋጁ አንቀጽ 27 ከንዑስ አንቀጽ (9) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (10) እና** (11) ፊደል ተራ (ሀ)፣(ለ)፣(ሐ)፣(መ)፣(ሠ) **ተጨምሯል፡፡**

(10) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ካፒታል ለማሳደግ አባል ላልሆነ ሰው ዕጣ መሸጥ ይችላል፡፡ ሆኖም የሚሸጠው ዕጣ ከታወጀው ጠቅላላ ዕጣ ከ10 ከመቶ መብለጥ የለበትም፡፡

(11) የኅብረት ሥራ ማህበር ዕጣ የገዛ አባል ያልሆነ ሰው የሚከተሉት መብትና ግደታዎች ይኖሩታል፡፡

ሀ) በገዛው የዕጣ መጠን መሠረት የትርፍ ክፍፍል ያገኛል፣

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከከሰረ የኪሳራው ተጋሪ ሊሆን አይችልም፣

ሐ) የገዛው እጣ እንዲሰጠው በጠየቀ 60 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የማግኘት፣

መ) የመምረጥና የመመረጥ መብት አይኖረውም፣

ሠ) የኅብረት ስራ ማህበሩን ህልውና የሚያሳጣ ስራ ያለመስራት፣

13/ **የአዋጁ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ (1) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (1) ተተክቷል፡፡**

(1) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የጠቅላላ ጉባዔ ማድረግ አለበት፡፡

14/ **የአዋጁ አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ (2) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (2) ተተክቷል ፣**

**(2)** ለመጠባበቂያ ከተቀነሰ በኃላ የተጣራ የትርፍ ክፍፍል 3 ከመቶ ለኅብረት ሥራ ፈንድ የሚውል ሲሆን ቀሪው ስልሳ ሰባት ከመቶ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በሚወስነው መሰረት የሚከፋፈል ይሆናል፡፡

15/ **የአዋጁ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ (1) ተሰርዞ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አቀጽ (1)፣(2)፣(3)እና (4) ተጨምረዋል፣ ነባሮቹ ንዑስ አንቀጽ (2)፣(3)፣(4) እና (5) በቅድም ተከተላቸው (5)፣ (6)፣ (7) እና (8) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡**

(1) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የኦዲት ወጪውን ሸፍኖ ሂሳቡን ኦዲት ማስደረግ አለበት፡፡

(2) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ ኦዲት የሚደረገዉ በኅብረት ሥራ ሊግ፣ በኦዲት ሙያዎች በተደራጀ የኅብረት ሥራ ማህበር ወይም ህጋዊ የኦዲት ፈቃድ ባለው ሰው ነዉ፡፡

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገዉ ቢኖርም አግባብ ያለው ባለስልጣን በልዩ ሁኔታ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ይችላል፡፡

(4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያለው ባለስልጣን የኦዲት ሂደት ክትትል እና ቁጥጥር የሚያደርግበት መመሪያ ያወጣል፡፡

16/ ከ**አዋጅ አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ (4) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) ተጨምሯል፡፡**

(5) አግባብ ያለው ባለስልጣን የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን መለኪያ ስታንዳርድ በማወጣት ኢንስፔክት ያደርጋል፡፡

(6) አግባብ ያለው ባለስልጣን የኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ በተከሰቱ የአሰራር እና የሕግ ጥሰቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡ስለዝርዝር አፈጻጸሙ በሚኒስትሮች ምክርቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

**17/ የአዋጁ አንቀጽ 75 ከንዑስ አንቀጽ (3) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አቀንጽ (4) ተጨምረዋል፡፡**

(4) በዚህ ማሻሻያ አዋጅ መሰረት የተቀላቀሉ ወይም እንደገና የተደራጁ የኅብረት ስራ ማህበራት እንደ አዲስ መመዝገብ አለባቸዉ፡፡

**3. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**<u>አዲስ አበባ--- 2018 ዓ.ም</u>**

**<u>ታዬ አጽቀስላሤ</u>**

**<u>የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክረሲያዊ</u>**

**<u>ሪፐብሊክ ፕሬዘደንት</u>**

**Proclamation No. --------/2025**

**Cooperative Societies (Amendment) Proclamation**

WHEARAS our cooperatives have low capital and members and are fragmented; it has become necessary to enhance bargaining power in market participation and the economic activity through mergers and consolidations.

NOW THEREFORE, in accordance with Article 55(6) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

1. **Short Title**

This proclamation may be cited as **"Cooperative Societies (Amendment) Proclamation No.--/2025**".

**2. Amendment**

**1/ Sub Article (10) of Article 2 is deleted and replaced by the following new sub article (10):**

**(10)"Member"** means an individual or a primary cooperative society or union or federation or institution with legal entity that has applied for membership and has been admitted by the cooperative in accordance with the cooperative's rules of procedure and has met the membership criteria prescribed by the cooperative.

2/ **Sub Article (20) of Article 2 is deleted and replaced by the following new sub article (20):**

**(20) ''Appropriate authority''** means the Ethiopian cooperative commission or an organ established at regional levels to execute the Cooperative Societies Proclamation, lead and regulate the Cooperatives.

3/ **New sub-articles 24 and 25 are added after sub-article 23 of Article 2 of the Proclamation, and the existing sub-articles 24, 25 are renumbered as 26 and 27, respectively.**

(**24) "Merging"** means amalgamating a cooperative society with another cooperative society with a similar objective and function, provided it meets necessary requirements, and after which it ceases to exist.

(25)**"Special audit"** means that when it is believed that the cooperative cannot cover the audit costs, or when it is decided to dissolve, or when it is necessary to verify the audit conducted, or when it is ordered by a court, or when there are risks and propositions, an appropriate authority conduct audit by covering the audit costs under special circumstances.

4/ **Sub-article 5 of Article 7 is deleted and replaced by the following new sub article(5) and new sub article (6) is added.**

(5) A comprehensive performance directive shall be issued to determine any primary cooperative societies organized at the kebele or institutional, or district level, based on the specific circumstances of the region, the type of cooperative, the nature of the work, or its economic feasibility. The details shall be prescribed by a directive.

(6) primary cooperatives or unions, or federations organized in the same functions, may merge.

(7) The details of the implementation of sub article (5) and (6) of this Article shall be prescribed by the directive

**5/ The title of Article 9 of the Proclamation is amended as follows:**

(9) Name and working area of the cooperatives

**6/ New sub-articles 6, 7, 8 are added after sub-article 5 of Article 9 of the Proclamation.**

(6)Any cooperative society shall have its working area specified in its rule of procedure.

(7) Any cooperative society shall revise its working area upon approval of the appropriate authority

(8) Directive shall be issued regarding the names and working areas of cooperatives.

**7/ Sub-article 2 of Article 14 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub article(2) , and next to sub-article 3, new sub-articles (4) and (5) are added.**

**( 2)** A cooperative union shall be organized at the zone or region or federal level, based on the specific circumstances of the region, the type of cooperative societies, the nature of the work, or its economic feasibility. The details shall be prescribed by a directive.

(4) Cooperatives societies engaged in the same type of agricultural production shall be organized into only one union at the zonal level.

(5) Regions without a zonal structure shall organize into only one union at the regional level.

**8/** Sub-**Article 4 paragraph (a) of article 21 is deleted and replaced by the following new paragraph (a):**

**a)** Arrange audit services for members of cooperative societies and unions,

**9/ A new sub-article 11 is added, after sub-article 10, Article 21 of the Proclamation.**

(11) The management or board of cooperative societies may use advisory experts to advise them. The details shall be prescribed by a directive.

**10/ New sub-articles (2) paragraphs (a),(b),(c) and sub article (3) are added after sub-article 1 of Article 23 of the Proclamation, and existing sub-article (2) is renumbered as sub-article 4.**

(2) Cooperatives societies conducting joint investment with the private sector shall request a special resolution, and the organizational objectives and functions of cooperatives societies, joint investment focuses on the following investment areas;

**a)** Agricultural production, or Agro- or marketing, or manufacturing industry or mechanization sector

**b)** Transportation, or infrastructure, or Finance, sector

**c)** Energy supply, or Construction, sector

**d)** community watershed development or climate change resilience or tourism service

(3) Cooperatives societies conducting joint investments with the private sector shall be established with a contractual agreement and authenticated by a responsible body.

11/ **A new Sub-Article (3) and (4) is added after Sub-Article (2) of Article 24 of the Proclamation, and Sub-Article 3 is renumbered as Sub-Article 5.**

(3) Institutions may become members of primary Savings and Credit cooperatives. The appropriate authority shall issue a directive for its implementation.

(4) **"Institution"** means a governmental or non-governmental service provider or producer institution with legal personality that meets the membership requirements and can become a member of a primary savings and credit cooperative society.

12/ **New sub-articles 10, 11 (a, b, c,d,e,f) have been added after sub-article 9 of Article 27 of the Proclamation.**

(10) Any cooperative society may sell shares to a non-member to increase its capital. However, the number of shares sold shall not exceed ten percent of the total number of shares declared.

(11) A non-member who has purchased a share of the cooperative societies shall have the following rights and obligations:

a) shall receive a dividend based on the amount of the share purchased,

b) the cooperative goes bankrupt, shall not be a shareholder of the bankrupt,

c) Requesting to obtain the purchased share, have the right to obtain within 2 months

d) Shall not have the right to vote or be elected,

e) Obeying of cooperative societies' bylaws

f) prohibition of an act against the legal personality of a cooperative society

**13/ Sub-Article 1 of Article 33 of the Proclamation shall hereby be amended as follows:**

(1)Any cooperative shall hold a general assembly meeting at least once a year.

**14/ Sub-article 2 of Article 45 of the Proclamation is amended as follows:**

(2) After deduction for reserves, the net profit shall be allocated three percent to the Cooperative Fund, and the remaining sixty seven percent shall be distributed based on the decision made by the General Assembly of the cooperative.

15/ **Sub-article 1 of Article 50 of the Proclamation has been revoked and repealed new sub-articles 1, 2,3 have been added, while sub-articles 2, 3, 4 and 5 have been renumbered as 4, 5, 6 and 7, respectively.**

(1) Any Cooperative society must have its financial statements at least once in a year, by covering the cost of the audit.

(2) Cooperative society's financial statements shall be audited by a League or a professional auditor organized through a cooperative or a firm with a legal auditing license.

(3) Without prejudice to sub-article 2 of this Article, the appropriate authority may, in special circumstances, audit the financial statements of cooperative societies.

( 4) Without prejudice to sub-article 2 of this Article, the appropriate authority shall issue a directive for overseeing and supervising the audit process.

**16/ The following sub-articles 5 and 6 are added after Article 52, Sub-article 4 of the Proclamation.**

(5) The financial activities of Savings and Credit Cooperatives shall be inspected through site standards.

(6) The appropriate authority shall take corrective measures against procedural and legal violations committed by cooperatives. The Ethiopian Cooperative Commission shall issue a directive for its detailed implementation.

**17/ A new sub-article 4 is added after sub-article 3 of Article 75 of the Proclamation.**

(4) Based on this amended proclamation, a merged or reorganized Cooperative society shall be re-registered. Details, directives shall be issued.

**3. Effective Date**

This proclamation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Addis Ababa--- 2025**

**Taye Atsekesilassie**

**President of the Federal Democratic Republic of Ethiopia**

**Republic of Ethiopia**